# የኩርፊያ ስልቻው መቼ ነው የሚሞላው?

ታደገ tadmeng@yahoo.com

የአገራችን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ታሪክ እጅግ አስገራሚ እየሆነ መጥቷል፡፡ ከአመሠራረታቸው ስንነሳ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚመሰረቱት የሕዝብና የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ሳይሆን የግለሰቦችን ጥቅማ ጥቅም ለማስጠበቅ ነው ብል አልተሳሳትኩም፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ ፓርቲዎች ሕዝባዊ መሠረት የላቸውም፡፡

ሕዝባዊ መሠረት የሌላቸው መሆናቸው በርካታ ችግር ሲገጥማቸውና ችግርም ሲፈጥሩ ከተስተዋሉ ሰነባብተዋል፡፡ መደራጀት አፍታም ሳይቆዩ ደግሞ መበታተን፡፡ ይህ የተቀዋሚ ፓርቲዎች የመደራጀትና የመበታተን አባዜ እስካሁን አብሯቸው ሊዘልቅ ችሏል፡፡

በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት የተፈጠሩት የፓርቲዎች ጥምረት ለሕዝብ መነቃቃትንና አዲስ የፖለቲካ መንፈስን የፈጠረ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የተፈጠረው ጥምረት በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ የወራት ዕድሜ እንኳን ሳያስቆጥሩ መበታተን ዕጣ ፋንታቸው ሆነ፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው የተባለውን አዲስ የፖለቲካ ባህል ይዘው ወደ ምርጫ የመጡት ተቃዋሚዎች /ቅንጅት/ በሚል ስያሜ ወደ ምርጫ ቢገቡም ከምርጫ በኋላ ብዙ ርቀት መራመድ አልቻሉም፡፡ ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም ሲሉ የተደራጁ ቢሆን ኖሮ ሕዝብ በድምፅ የሰጣቸውን የምክር ቤት መቀመጫ የሕዝብ ውክልና መሆኑን ተገንዝበው የጠራ ፖሊሲና ስትራቴጅ ቀርፀዉ ወደ ተግባር መግባት በቻሉ ነበር፡፡

ሁሉም በየፊናቸው ለግል ዝናና ለስልጣን ሽኩቻ መሯሯጥን ተያያዙት ; የተነሱለትን አላማ በመርሳት የግል ጥቅማቸውን ለማሳደድ መንገድ መጠራረግ ጀመሩ; ባለፈው ምርጫ 1997 አንዴ ህጋዊ ሲያስፈልግ ደግሞ ህገ ወጥ በመሆን  መላቅጡ ሲጠፋቸው ከቆዩ በሁዋላ እንኳን ተወዳድረው ያገኙትን ድምፅ ይዘው ፓርላማ እንዲገቡ ሲጠየቁ አሻፈረኝ በማለት የአመፅ መንገድን መረጡ ፡፡በሰላማዊ መንገድ ድምፅ የሰጣቸውን የአዲስ አበባን ህዝብም ሜዳ ላይ ጣሉት ; ርካሽ ተወዳጅነትንና ታዋቂነትን ለማትረፍ የሚያደርጉት መሯሯጥ የቆሙለትን ዓላማ አስረሳቸው;በዚህ መልኩ መጨረሻቸው መበታተን ሆነ ማለት ነው;

የሚገርመው ነገር ደግሞ ስለመበታተናቸው ሁሌም የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ተመሳሳይነት ያላቸው መሆናቸው ነው; እነዚህም "ግልፅነት የለም ፤ የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አልተከበረም ፣ የጥቂት ግለሰቦች አምባገነናዊነትና ፀረ ዴሞክራሲያዊነት  ነግሷል ወዘተ " የሚሉት ይገኙባቸዋል ፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም ቢሆን እርስ በእርስ ከመወነጃጀል ባለፈ "የችግሩ ምንጭ ይሄ ነው ፡ወይም እኔ በዚህ መልኩ ስህተት ሰርቻለሁና በዚህ መልኩ ይስተካከል" ብሎ ያመነም ይሁን ለችግሩ መንስኤ ራሱን ተወቃሽ የሚያደርግ ተቃዋሚ ፓርቲ ማየት አለመቻላችን ሌላው አስገራሚ ክስተት ነው፡፡

ያለፈውን በዚህ ልተወውና @ የ 2002 ዓ.ም አገራዊና ክልላዊ ምርጫ በወራት የሚቆጠር ጊዜ በቀረበት ወቅት አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ለምርጫው ዝግጅት ማድረጋቸውን በመዘንጋት በጭፍን ጥላቻ የፖለቲካ ምህዳር ጠበበብን፣ የፕሬስ ነፃነት የለም፣ ቢሮአችን ተዘግቷል ወዘተ በማለት ጉንጭ አልፋ ክርክራቸውን ማድመጥ የተመለደ እየሆነ መጥቷል፡፡

ይህ ጉንጭ አልፋ ክርክር በመቀጠሉና የ2002 ምርጫ ያለ በቂ ዝግጅት መቃረቡ በርካቶችን እርስ በእርስ እያናከሰ ይገኛል፡፡ የጊዜ ወርቅነትን የተረዱ አይመስሉም፡፡ ይህ ነው የሚባል ዝግጅት ሳያደርጉ ጊዜም እንደዘበት አስቀምጧቸው ነጉደ፡፡

ለምርጫው ሂደት ዝግጁ ሆኖ አለመገኘት ደግሞ ሌላ ጣጣ ማምጣቱ አልቀረም፡፡ ብጥብጥ፣ እርስ በእርስ መናካከስ፣ በስነምግባር አልባነት መዘላለፍ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተቀባይነት የሌለው ምክንያት መደርደር ተጀምሯል፡፡ለድርድር የማይቀርቡ የሕግ የበላይነት ጉዳዮችንም እንደድርድር አጀንዳ ለማቅረብ ተሞክሯል።ቀድሞውኑ ገመናቸውን መሸፈን ሲያቅታቸው ሰበብ መደርደሩ ሊመጣ እንደሚችል ሁሉም የጠበቀው ጉዳይ ነበር፡፡

የማይደበቀው ገመናቸው ሲጋለጥባቸውና ፀረ- ዴሞክራሲያዊ አካሄዳቸው ሊያስማማቸው ባለመቻሉ በየጊዜው እርስ በእርስ መበጣበጥ፣ አንዳቸው አንዳቸውን ለማዳመጥ ትዕግስት ማጣታቸው፡ በቃላት እንጅ በተግባር ማሳየት አለመቻላቸው በሕዝቡ ዘንድ ተዓማኒነትን እያሳጣቸው መጥቷል።

ይህ አልደበቅላቸው ያለ መጥፎ ገመናቸው በየጊዜው ሲያጋልጣቸውና እንደ እርኩስ መንፈስ የተጠናወታቸው የኩርፊያ አባዜ አለቃቸው ብሎ በየጊዜው የስብሰባ መድረክ እየረገጡ ይወጣሉ፡፡ በቅርቡ የተከሰተውም ይኸው ነው፡፡ አንዳንድ ድርጅቶችና ኤምባሲዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ፓርቲዎችን ለማወያየት ፈልገው መድረክ ሲያመቻቹ እገሌ የሚባል ፓርቲ ከተሣተፈ እኛ እርሱ ባለበት አንሳተፍም በማለት ፀረ-ዴሞክራሲያዊነታቸውን ገሃድ አውጥተዋል፡፡

‹‹የእኔን አቋም ካልደገፍክ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ መነጋገርም ሆነ መወያየት አትችልም፤ አንፈቅድም›› ማለት የለየለት አምባገነንነት ነው፡፡ በዚህ አይነት  አምባገነንነት እንዴት ነው የተለያየ ፍላጎት፣ ባህል፣ ወግ፣

ሀይማኖት፣ ቋንቋ አመለካከት ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊመሩ የሚችሉት፡፡ አስተውሎ ለተመለከተው ነገሩ ግራ አጋቢ ነው፡፡”

ሰሞኑን ደግሞ በምርጫ ወቅት የሚነሱ አላስፈላጊ ግጭቶችን ለመቀነስ፣ ነፃና ፍትሐዊ የሆነ የምርጫ ውድድርን ለማበረታታትና የመብት ጥሰትን ለመከላከል የሚያግዝ ሰነድ አውሮፓ በሚገኝ ኢንተርናሽናል ኢንስቲትዩት ፎር ዴሞክራሲ ኤንድ ኤልክቶሪያል አሲስታንስ /IDEA/ በተሰኘ ተቋም ተዘጋጅቶ ኢህአዴግና ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲወያዩበት መድረክ ተመቻችቶ ድርድር እየተደረገ ነው፡፡

በስነምግባር ደንቡ ላይ የተደረገው ድርድር በአገሪቱ በተደረገው የ1997 ዓ.ም. ምርጫ ወቅት የተከሰተውን ነውጥና ሁከት ደግም እንዳይከሰት ለማድረግና ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምርጫው ፍትሃዊነት የበኩላቸውን እንዲወጡ ለማድረግ ነው፡፡

ሆኖም ግን በዚህ የስነምግባር ደንብ ድርድር ወቅት በተለይ መድረክ የተባለው ድርጅት ድርድሩን አቋርጦ እንደወጣ በሚድያ ተከታትለናል። ይህ ፓርቲ በድርድር ወቅት ተጨማሪ ጊዜ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄ እንዳቀረበና፣ የውይይቱን ጠቃሚነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ ቀናት ቢፈቀድም ሌላ ጣጣ ከጀርባው ይዞ መጣ፡፡ ድርድር ማድረግ የምፈልገው ከኢህአዴግ (ከገዥው ፓርቲ) ጋር ብቻ ነው የሚል፡፡

ታድያ ይህ አይነት አካሄድ ምን የሚሉት ፍልስፍና ነው፡፡ አገራዊ ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ሁሉም የሚመለከታቸው ፓርቲዎች ባሉበት ድርድር መደረግ ሲገባው  እንዲህ አይነቱን አካሄድ አልቀበለም ማለት ፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ነው፡፡ አሁን በተመሰረቱት የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ በርካታ የደርግ ሹማምንቶች ይገኛሉ፡፡ አሁን ኢህአዴግ ከደርግ ጋር በነበረው ቁርሾ የተነሳ ከእናንተ ጋር ወይም የደርግ ሹማምንት ካሉበት ፓርቲ ጋር አርደራደርም የሚል አቋም ቢያንፀባርቅ ኖሮ ህዝብ

ምን ይል ነበር) የአሁኖቹ አኩራፊ ፓርቲዎችስ ምን ይሰማቸው ይሆን ? የሚል ጥያቄ በአዕምሮዮ ብልጭ አለብኝ፡፡

የምርጫ ስነምግባር ደንቡ የሚዘጋጀው ለተወሰኑ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆን በምርጫው ለሚሳተፉ ሁሉም ፓርቲዎች መሆኑ እየታወቀ እነ እገሌ የሚሳተፉ ከሆነ አንሳተፍም የሚል አባዜ ምን የሚሉት ነው? እስኪ መቼ ነው እነዚህ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የመነጣጠል ሴራ አካሄዳቸው ከራሳቸው ላይ ወርዶ ችግራችንን በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታት በጋራ እንወያይ የሚል ቅዱስ መንፈስ ያደረበት አክሊል የሚደፉት? ቀኗን ናፍቀናል፡፡

የመድረክ ተወካዮች ታድያ ከላይ የጠቀስኩት አይነት ምላሽ ሲሰጣቸው ስብሰባውን ረግጠው፣ ድርድሩንም አቋርጠው ወጥተዋል፡፡የድርድር መድረኩ የተዘጋጀው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድን ለማንፀባረቅ ሳይሆን የዴሞክራሲ ባህልን ለማጎልበት መሆኑን የተረዱት አይመስለኝም፡፡

ይህን ድርድር አቋርጠው የመውጣታቸው ጉዳይ ከ1997 የቅደመ ምርጫ ወቅት ሲያራምዱ ከነበሩት የሕገ ወጥነትና ህጋዊነትን እያጣቀሱ መጓዝ ጋር ልዩነት የለውም፡፡በወቅቱም በመጀመሪያ እሳቱን አቀጣጥለው ወደኋላ የሸሹና ከቅጣቱ ያመለጡ ግለሰቦች ነበሩ፡፡ እነዚያ ግለሰቦች በአሁኑ መድረክ ውስጥ ሌላ የጥፋት መረብ መዘርጋታቸውን በተግባር እያሳዩ ነው ፡፡ ያ ሁከትና ብጥበጥ አስነስቶ በኋላ ገሸሽ ብሎ የመደበቅ ድራማ አሁንም አልበቃቸው ብሎ እየደገሙት ይገኛሉ፡፡

በጥቅሉ የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች የትግል ጉዞ የትላንት ስህተታቸውን በማረም ወደ ሰላማዊ ትግል ከመመለስ ይልቅ ዛሬም ያለፈ ስህተቻውን እየደገሙት ይገኛሉ ማለት ይቻላል፡፡ ፓርቲዎች በተለያዩ ጊዜያት ገዥውን ፓርቲ በጥብቅ የሚቃወሙባቸውን ተግባራት/ጉዳዮች/

ሳይቀር ራሳቸው እየፈፀሙት ናቸው፡፡ ‹‹ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል›› እንዲሉ፡፡

ለዚህም ጥሩ መገለጫ ይሆን ዘንድ አንድ አብነት ላንሳ፡፡ የአንድነት ፓርቲ ሠሞኑን በአዋሳ ባካሄደው ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንዳይገኝ ከልክለዋል፡፡ ይህ ደግሞ የሕዝብ መረጃ የማግኘት መብትንና ነፃነትን በገሃድ ሲደፍቁት ታይተዋል፡፡ ጋዜጠኞችን በአደባባይ በመስደብና አመናጭቀው በማዋረድ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን የሕዝብ መረጃ የማግኘት መብት በግልፅ ተቃወመዋል፡፡

በመጪው ምርጫ ማንም ያሸንፍ ማን ሰላማዊ፣ ነፃና ፍትሃዊ ይሆን ዘንድ የኢትዮጵያ ህዝብ ምኞት መሆኑን ሁሉም ፓርቲዎች ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ ምርጫው ከሁከትና ከብጥብጥ የፀዳ እንዲሆን ደግሞ በስልጣን ላይ የሚገኘው ፓርቲ ወንጀሎች ሲፈፀሙ ቅፅበታዊ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የተለመደውን ሆደ ሰፊነት ሊያሳይ ይገባዋል፡፡

የአገራችን የተቃዋሚ ፓርቲዎችም ተነጋገሮ ከመተማመን ይልቅ ልዩነትንና መጠፋፋትን፣ ከድርጅት ጥቅም ይልቅ የግል ጥቅምንና ዝናን መምረጣችሁ በመጪው ጊዜ አትኩሮታችሁ የምርጫ ፉክክሩ ላይ እንዳይሆን ያደርጋልና ጠንቀቅ ማለቱ ያሻል፡፡ ከዚህ ይልቅ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች የማስተላልፈው መልእክት ህዝብን የሚስብ ተጨባጭ ፖሊሲና ፕሮግራም ቀርፆ በሰላማዊ መንገድ ለምርጫው መወዳደሩ ይበጃል እላለሁ ፡፡ ቸር እንሰንብት!